# ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ!!!

ከዓሣዬ

ለዴሞክራሲ መብት ለኔ ህልውና የታደጉኝን
ብዙ ሺህ ልጆቼን በፋሺሥት ጭካኔ የረሸኑብኝ
ሁለተኛውን ዙር ልክ እንደ ትላንቱ ዛሬም ሊደግሙኝ
ዳግም ጥምረት ፈጥረው ሊበታትኑኝ
በቁሥሌ በርበሬ ሲጨምሩብኝ
ፋሺሥት ግም ሞት እሣት ሲዶልቱብኝ
ሰምቼ በእሣት ሲሞከሻሹና ሲደነፉብኝ
በሲቃ ሰቆቃ ሆዴ ተንዘፍዝፎ እዬተማጸንኩኝ
ልክ እንደ ክርሥቶስ ጩኸቴን ብትሰማኝ
አንጀቴን ኣሥሬ እጆቼን ዘርግቼ ይኸውና አልኩኝ
ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ እንባ እየረጨሁኝ!!!
ጽዋውን ኣጋጭተው ፋሺሥትና እሣት
ኢትዮጵያን ኣጋይተው ዳግም ሊበትኗት
ጠባብ ባንዳ አንጃ ጥምረት ፈጥረውባት
ባላገር ሊሆን ባዳ!
የባዕድ ቅጥረኛው ባንዳ ሊሾምባት
ታሪኳ ተፍቆ!
እሷነቷ ጠፍቶ ልትሆን የሣት ዕራት
እንደ ጭዳ በሬ
ካራ እየሣሉ ቆራርጠው ሊጥሏት
ዕዝ ተቀብለዋል ከባዕዳን ጠላት
ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ኢትዮጵያን አድናት።
01/01/2014 G. C.